# ግልጽ ደብዳቤ ለአቶ ታምራት ላይኔ
## ግልባጭ ለተቃዋሚ ድርጅቶች በሙሉ

## ከአሲንባ የውይይት መድረክ

ለአሥራ ሁለት አመታት ከወያኔ ግብረ አበሮችህ ጋር በመሆን ባቋቋምከው እስር ቤት ውስጥ ከርመህ በመፈታትህ ቤተሰቦችህን እንኳን ደስ አላቸው እንላለን። መቼም ሰብአዊ ተፈጥሮአችን እያስገደደን በአንተ ምክንያት በቤተሰብህ ላይ የደረሰውን ሰቆቃ ማየት ያሳዝነን እንደነበር በዚህ አጋጣሚ ልንነግርህ እንወዳለን።ሃገራችን ሕፃናት ሳይቀሩ የእሰር ቤትን አስከፊነት በመገንዘብ በወያኔ እስር ቤቶች በግፍ የሚማቅቁ ወላጆቻቸውን ለማስፈታት ጥረት የሚደርጉበት የአስተዳደር ዘመን በመድረስዋ እያንዳንዳችን ከልባችን ሃዘን ይሰማናል። የአንተም ልጅ ይህ ዕጣ ደርሷት ባለፈው ግዜ የፃፈችውን ደብዳቤ ከድ'ነረ ገፆች ስናነብ ፍፁም የሆነ ሃዘን ተሰምቶን ነበር ።

ከተፈታህም በኋላ ፊትህን ወደ እግዚአብሔር የመለስክ መሆኑን ስንሰማ ይህንን ግልፅ ደብዳቤ ለአንተ በግልባጭ ደግሞ ለተቃዋሚ ድርጅቶች ለመጻፍ ተገደናል። ከእኛ የበለጠ አንተ እንደተረዳኸው የኃጢያት ሥርየትም የሚገኘው የልብን በልብ አምቆ የይስሙላ ንግግር በማሳመር ሳይሆን በልብህ ውስጥ የደበቅካቸውን በደሎች ሁሉ አውጥቶ ምስክርነትን መስጠትን የግድ ይላል።ጽድቅ በግማሽ አይገኝም። መለወጥም ከልብ ሊሆን ይገባል። እንባህ እየፈሰሰ ቃለ እግዚአብሔርን ስትናገር ስንመለከት እውን ይህ ሰው በሕዝቡና በሃገሩ ላይ የሰራው ከሃዲነት ልቡን ሰብሮት ነው ወይ እንዲህ የሚንሰቀሰቀው? ወይስ በፊት የሠራውን በደል ሕዝቡ እንዳይቆጥርበት ለማደናገር የአዞ እንባ ነው የሚነባው ማለታችን አልቀረም።

አዎ እስር ቤት ይፈትናል።ጠንካራና ትዕግስተኛም ያደርጋል።አርቆ ማስተዋልን ፣ለእውነት መቆምን፣ በግፍ ለተጠቁ መከራከርን፣ ያስተምራል።በእስር ቤት ውስጥ በአሳሪዎች የሚደርስ ግፍ ልብን ይሰብራል ብትለን ለማመን ያዳግታል።በእኛ አስተሳሰብ ልብን የሚሰብረው በሃገርና በወገን ላይ የተሰራ ግፍ ነው። በሌሎች ንፁሃን ላይ የአደረስከው አሰቃቂ ተግባር ነው። በዘር እየከፋፈሉ ሕዝብን ማጋጨት ነው ። ንፁሃንን እያፈሱ ወደ እሰር ቤት ማጎር ነው።በተለይ እንደ አንተ ከፖለቲካው የወዲያኛው ጎራ ለነበረ ሰው ፣ ከአሳሪ ፈቺነት ፣ ከፈራጅነት ጎራ ለነበረ ሰው ፣ እስር ቤት የደረሰብኝ መከራ ልቤን ሰበረው ብትል ልናምንህ አንችልም።ልብን የሚሰብረው በስልጣን ላይ በነበርክበት ወቅት በሌሎች ላይ ስታደርሳቸው የነበሩት አስቃቂ ተግባሮች ናቸው ። እነዚህ ተግባሮችህ ከመቼውም የበለጠ እንቅልፍ እንደሚነሱህ የታመነ ነው። አዕምሮህንም ያውኩታል። ታዲያ ከዚህ የጭንቀት ኑሮ የሚያወጣህ ግን አንድ ነገር ነው እሱም በልብህ ውስጥ የታጨቀውን አዋኪ መንፈስ አውጥተህ ስትናዘዘው ነው። በጀመርከው የሥርየት መንገድ እውነት በሆነ መልኩ በመፈፀም በሌሎች ስታደርገው የነበረውን በደል አውጥቶ በመናዘዝ ነው።

በዚህ በአንተ ላይ በደረሰው ቤተሰቦችህና የሚወዱህ ምን ያህል እንደተጨነቁ የምታውቀው ነው ብለን እናምናለን።አንድ ሰው የታሰረበት ቦታ እንኳ ታውቆ ዘመድ አዝማድ ቀለቡን እያቀረበለት እስር ምን ያህል አስከፊ መሆኑን የተገነዘብከው ይመስለናል።ለብዙ አመታት እናንተ ባዘጋጃችሁት እስር ቤት ውስጥ በድብቅ ቦታ የታሰሩትን ዞር ብለህ ልታስባቸው የሚገባው ይህ "ንሰሃ ዘመን" ብለህ በምታነባበት ወቅት ነው። ምን ያህል ስቃይ ውስጥ አንዳሉም ለአንተ የሚደበቅ አደለም። በየቦታው በአንተ መሪነት የተዘጋጁትን እስር ቤቶች ፣ መሰቃያ ቦታዎች በሚገባ ታውቃቸዋለህ።

በዚህ ደብዳቤችን ልናሳስብህ እምንወደው ነገር ቢኖር አንተን ከበደል የሚያጠራ እኛን እንቅልፍ ከማጣት ሊያድን የሚችል ወገኖችችንን አርነት የሚያወጣ ታላቅ ጉዳይ ነው። ስልጣን ላይ በነበርክበት ወቅት በወያኔ እስር ቤት ውስጥ በድብቅ ያሰራችኋቸውን የኢሕአፓ አባላትን ለአንድ አፍታ እንደማትዘነጋቸው ተስፋ አለን። እንደነ ጸጋዬ ደብተራውን የመሰሉ ኢትዮጵያውያን በወያኔ እስር ቤት ውስጥ አሁንም ደብዛቸው ጠፍቶ ይገኛል። የእነዚህ የኢሕአፓ አባለትም ቤተሰቦቻቸው መድረሻቸውን ለማወቅ በጉጉት ይጠብቃሉ ብንልህ እንግዳ ነገር አይሆንብህም።የልጅህን ሰቀቀን የምታስታውሰው ነው ብለን እናምናለን። እነዚህ የኢሕአፓ አባላት የት እንዳሉ ከአንተ የበለጠ የሚያውቅ የለም ። የቤተሰቦችህን ችግርና ሰቆቃ የቀመስከው በመሆኑ የሌሎች ቤተሰቦችንም ስቃይና ሰቆቃ በዚሁ አንፃር በተለይ አሁን የንሰሃ እንባ በምታነባበት ወቅት ለመገመት የሚከብድህ አይመስለንም። ይህንን የኢሕአፓ አባላትን በወያኔ የደረሰባቸውን ሰቆቃ ግልጽ አድርገህ ለቤተሰቦቻቸው ብታስረዳ በዚህ በጎ ምግባር ለብዙ ዓመታት በስቃይ ላይ የከረሙትን ቤተሰቦች ሊፅናኑ ይችላሉ ብለን እናምናለን።እንዲሁም የአዕምሮ ጭንቀትህም የሚቀረፍልህ ይሆናል።አለበለዚያ ግን እስከመጨረሻው የሕይወት እስትንፋስህ የታሪክ ተወቃሽነት ፣ የኀሊና ተከሳሽነት እንደማታመልጥ ልናሳስብህ እንወዳለን።

በዚሁ ግልፅ ደብዳቤችን ደግሞ የተቃዋሚ ድርጅቶችንም ጭምር ልናሳስብ የምንወደው አለን። እነ አቶ ስዬ አብርሃ ከወያኔ እስር ቤት ወጥተው እንደ ወያኔ ተቃዋሚ ወደ ሰሜን አሜሪካ ጉዞ ባደረጉበት ወቅት በተቻለን መጠን የእነዚህ ደብዛቸው ያልታወቀውን የኢሕአፓ አባላትን ጉዳይ በሚመለከት በሕዝብ እንዲጠየቁ ጥረት አድርገናል። ቢሆንም ሌሎች የተቃዋሚ ድርጅቶች አባላት ይህንን ጥያቄ አንስተው ለወያኔ መንግስት ፈላጭ ቆራጭ ለነበረው ለዚህ ግለሰብ ለመጠየቅም ሆነ ለማጋለጥ የሞከሩ አልነበሩም። በጣም የሚያሰገርመው ደግሞ ከኢሕአፓ የወጡ አንጃዎችም የነፀጋዬ ስም እንዳይነሳ ሲከላከሉ ነበር። እነዚህ አንጃዎች በሬዲዮ ጣቢያቸው በመቀስቀስ አቶ ስዬ እንደ ጀግና እንዲታዩ ያላሰለሰ ጥረት አድርገዋል። በእኛ አስተሳሰብ ስብዕናችን ቀድመው የወደቁትን ለፖለቲካ ጥቅም ብለን ልንረሳቸው መፍቀድ የለበትም። ይበልጥ እነዚህ መሰዋትነት የከፈሉት በክብር ቦታ በማይፋቅ ቀለም በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ሊፃፉ ይገባል ብለን እናምናለን።ከግል የፖለቲካ ጥቅም በመነሳት የእነዚህ ኢትዮጵያውያን

ሰብአዊ መብት እንዳይከበር ማድረግ የተናቀ የተዋረደ ስብዕናን መጎናፀፍ መሆኑን ሁላችንም ልናምን ይገባል።

ዛሬ እነ አቶ ስዬ አብረሃና መሰሎቻቸው የተቃዋሚ ድርጅቶች አስተባባሪ ለመሆንና ትግሉን እንደገና ለመግደል በሚራወጡበት ወቅት እነ ፀጋዬ ደብተራው ግን እነርሱ በከተቷቸው እስር ቤት ውስጥ እየማቀቁ መሆናቸውን መዘንጋት ምን ያህል አሳፋሪ ነው።አንዳንድ የተቃዋሚ ድርጅቶች የእነዚህ የኢሕአፓ አባላትን መድረሻ መጠየቅ ትግሉን እንደማዳከምና ወያኔንና ከወያኔ ወጣን የሚሉትን እነ ስዬን ማስቀየም ነው ብለው የሚምኑ አሉ። እውን ለሰብአዊ መብት መታገል ትግሉን ያዳክመዋል? ይህ እያንዳንዳችን ልናስብበት የሚገባ ጉዳይ ነው ። የእነዚህ የኢሕአፓ አባላት መድረሻ አለመታወቅ የኢሕአፓ አባላት ብቻ ችግር ነው ብለው የሚሉም ደካሞችም አሉ። የሰብአዊ መብት ጉዳይ የእያንዳንዱ የሃገሪቱ ዜጋ የእለት ተእለት ትግል እንጂ ከድርጅት ጋር የተያያዘ ሊሆን አይገባውም። ብዙዎቻችን ይህ የፓለቲካ እስረኞች ጉዳይ በራሳችን ላይ ካልደረሰ በስተቀር እንደ መወያያ ረዕስ አድርገን ልንወስደው፣ ለሌሎች መብት ተከራካሪነትን እንደ ትግል አድርገን አንቆጥረውም። በጣም የሚያሳፍረው ጉዳይ ዛሬም በራሳችን ላይ ሲደርስ እንኳ ሌሎችን ቀድመው በወያኔ እስር ቤት የሚንገላቱትን ስም ማንሳትን አንፈልግም።የነፀጋዬ ደብተራውን ስም ለመጥራት ፍርሃት ይዞን ስንቀጠቀጥ የታየንም አለን። የሚገርመው ስለ ሰብአዊ መብት እከራከራለሁ ይል የነበረው ድርጅት እንኳን ይህንን መጠየቅን አልደፈረም።የሰብአዊ መብት ጉዳይም በፍርሃት ተውጠን ለወያኔ እየሰገድን አንዱን አንስተን አንዱን አውቀን ረስተን የምንወጣው ትግል አደለም። ትግሉ ለምንወደውም ፣ ለማንወደውም ፣ ለሚግባባንም ፣ለማይግባባንም ፣ ለሚደግፈንም ፣ለሚቃወንም ፣ ለሁሉም ለሰው ዘር በሙሉ መቆምን የሚጠይቅ ነው። አሊያ በሰብአዊ መብት ትግል ውስጥ መግባት ለግል ተዋቂነት እንጂ ለትልቁ ቁምነገር አለመሆኑን ነው የሚሳየን። ወገናዊ የሆነ የሰብአዊ መብት ትግል አለ ብለን አናምንም። ማንም የሀገሪቱ ዜጋ ሰብአዊ መብቱ ሊከበር ይገባል። ይህንን የሰብአዊ መብትን አድሎ የጀመሩት ግለሰቦች በሀገራችን እድሜያችን ገፍቷል፣ አዘውንት ነን የሚሉት በመሆናቸው ትዝብትን አትርፈውበታል።

በጀርመን ውስጥ የናዚ ተቃዋሚ የነበረው ማርቲን ኒሙለር የተባለው ግለሰብ በናዚ ወቅት እስረኛ በነበረበት ግዜ የፃፈውን ስናነበው በወቅቱ በሃገራችን የደረሰውን አይነት ሁኔታን ያስታውሰናል።

ናዚዎቹ ኮሚኒስቶቹን ሲወስዱ ዝም አልኩኝ
ኮሚኒስታ አልነበርኩምና።
ሶሻል ድሞክራቶችንም ሲያስሩም ምንም አላልኩኝ
ሶሻል ዴሞክራት አልነበርኩምና።
የሰራተኛ ማህበር ተመራጮችንም ሲያስሩ ምንም አልተቃወምኩትም
የሰራተኛ ማህበር አልነበርኩምና።
አይሁዳውያንን ሲያስሩ አሁንም ፀጥታን መረጥኩ
አይሁድ አልነበርኩምና።
በመጨረሻም እኔን ሲወስዱ ለእኔ የሚጮኸልኝ ማንም አልነበረም።

ከዚህ የማርቲን ኒሙለር አባባል ብዙ እንማራለን። በአገዛዙ ላይ ወያኔ እስካለ ድረስ ሁሉም በየተራው እውነተኛ ተቃዋሚ እስከሆነ ድረስ ይደርሰዋል። እንደማርቲን አባባል የሰብአዊ መብት መጣስን ገና ከመጀመሪያው መታገል ያስፈልጋል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት የተከበረባት ሀገር እንድትሆን ካስፈለገ የእያንዳንዳችን አስተዋፅዖ አስፈላጊ ነው እንላለን። ዛሬ እነ ስዬ አብርሃም ሆነ እነ ገብሩ አስራት በማንኛውም የፖለቲካ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ከመፈቀዱ በፊት በወያኔ ውስጥ በነበሩበት ግዜ ስለ አጠፉት ጥፋት በማጋለጥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ መጠየቅ ይኖርባቸዋል ብለን እናምናለን። በየድብቅ የወያኔ እስር ቤት ውስጥ የከተቷቸውን ኢትዮጵያውያንን ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲገልጹ መጠየቅ ይኖርባቸዋል። ይህ ተክዶ ከነ ስዬ ጋር እንደተቃዋሚ ለመተቃቀፍ የሚደረገው ጥረት በእነ ስዬ መሪነት የተሰራውን ግፍ መጋራት ነው። በእየእስር ቤት ውስጥ የተዘጋበትን እስረኛን መካድ ነው ድጋሚ ማሰር ነው።

መለስን በግል መቃወም ብቻ ተቃዋሚ አያደርግም። የወያኔን ሚሥጢር አምቆ ይዞ ለዴሞክራሲ መታገልም አይቻልም። ሃጥያትን ደብቆ መንግስተ ሰማያትና መመኘት የበለጠ ኃጥያት ነው።ከአሣሪ ጋር አብሮ ለመብት መታገል አይቻልም። የሰብአዊ መብት ትግል አድልዎ ፍፁም ወንጀለኝነት ነው። እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉትን ስናስወግድ ነው እውነተኛ የሆነውን የሰብአዊ መብት ተከራካሪነት አርማ አንግበን ትግሉን የምንጀምረው።

ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ
የአሲንባ የውይይት መድረክ